# ደምብ/ሥርዓት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

ተዛማጅ ግብአቶች፦ CNA, CNB-RA, CND, EGC-RA, IPD-RA, IGT-RA
ኃላፊነት ያለበት ጽ/ቤት፦ የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ-
Deputy Superintendent of School Support and Improvement

## የመረጃ ቁሳቁሶችና ማስታወቂያዎች ትእይንት እና ስርጭት-
## Display and Distribution of Informational Materials and Announcements

I. ዓላማ

ከተማሪ ጋር ወደቤት ስለሚላኩ፣ ወይም በትምህርት ቤት ለእይታ ስለሚቀመጡ የታተሙ የመረጃ ወይም የማስታወቂያ ቁሳቁሶችን ስለማከፋፈል ወይም ትእይንት መመሪያ ስለመስጠት

II. ፍቺ - ትርጉም

**ለአትራፊነት ያልተቋቋሙ የማህበረሰብ ድርጅቶች ማለት በሞንትጎመሪ ካውንቲ እየሠሩ አትራፊ ስላለመሆናቸው ማስረጃ ዶኩመንት የሚያቀርቡ ናቸው።**

**የማህበረሰብ ድርጅት ወይም ቢዝነስ ማለት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ዉስጥ የሚሠራ ቡድን ወይም ቢዝነስ ነው።**

III. የቅደም-ተከተል ሥርአቶች

A. **በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ በመንግስታዊ ኤጀንሲዎች፣ በወላጅ መምህር ማህበራት/Parent Teacher Associations (PTAs)፣ እና በአንዳንድ የወላጅ-መምህር ድርጅቶች አማካይነት/Certain Parent-Teacher Organizations ለእይታ የሚቀርቡ እና በህትመት የሚሠራጩ የመረጃ ቁሳቁሶች/ማቴሪያሎች እና ማስታወቂያዎች**

1. ከሚከተሉት ድርጅቶች የሚቀርቡ የህትመት መረጃ ቁሳቁሶች እና ማስታወቂያዎች በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በቀጥታ ለተማሪዎች እቤታቸው በሚወስዷቸው ፎልደሮች-take-home folders፣ በእቃ መያዣ ቦርሣዎች-backpacks፣ ወይም በተመሣሣይ መንገድ ወይም በትምህርት አመቱ ዉስጥ ትምህርት ቤቱ በሚመድበው በማንኛውም ቦታዎች በጠረጴዛ ላይ ለእይታ፣የመጽሔት መደርደሪያዎች፣ወይም ተመሳሳይ ስፍራዎች ላይ እንዲሠራጭ ይፈቀዳል፦

    a) MCPS፦

    b) የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መንግስታዊ አካላት፣

    c) አገር አቀፍ ግንኙነት ያላቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በመሥራት ላይ የሚገኙ PTAs እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል PTAs፣ እና

d) በስፔሻል ኢጁኬሽን ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የወላጅ-መምህር ድርጅቶች/Parent-teacher organizations እና ከአገር አቀፍ PTAs ጋር በትስስር የሚሠሩ አማራጭ ማእከሎች።

**2. ድርጅቶች የህትመት መረጃ ቁሳቁሶችን/ማቴሪያሎችን እና ማስታወቂያዎችን ለትምህርት ቤት ማቅረብ ያለባቸው ለስርጭት ከተመደበው አምስት ቀን አስቀድሞ መሆን እንዳለበት** የትምህርት ቤት ሠራተኞች ይጠይቃሉ።

**3. የሠራተኞችን አስፈላጊ ሠዓት ለመቆጠብ የህትመት የመረጃ ቁሳቁሶች እና ማስታወቂያዎች በቅደምተከተል መደርደር ያለባቸው** ቁሳቁሶችን ለአያያዝ እንዲያመች **በ 30 ከምር መሆን አለበት።**

**B.** ከሌሎች የሚሰጡ የህትመት መረጃዊ ቁሳቁሶች እና ማስታወቂያዎች ለእይታ ማቅረብ እና ሥርጭት

1. ለትርፍ ካልተቋቋሙ የማህበረሰብ ድርጅቶች የሚቀርቡ የህትመት ቁሳቁሶች እና ማስታወቂያዎች በቀጥታ ለኤለመንተሪ ተማሪዎች እንዲሰራጭ የሚፈቀደው እቤታቸው በሚወስዱት ፎልደሮች፣ የመጻህፍት/ደብተር መያዣ ቦርሳዎች፣ ወይም በተመሣሣይ ሁኔታ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ እና በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ከአንድ ጊዜ የማይበልጥ ሆኖ በዓመት ከአራት ጊዜ የማይበልጥ መሆን አለበት። ለመካከለኛ ወይም ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንደዚህ አይነት ቀጥተኛ ስርጭት አይደረግም።

2. ሌሎች የማህበረሰብ ድርጅቶች ወይም ቢዝነሶች የሚያቀርቧቸው የህትመት ቁሳቁሶችን እና ማስታወቂያዎችን በ tables፣ magazine racks፣ ወይም የኤለመንተሪ፣ መካከለኛ፣ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ዓመት ውስጥ በሚመድቡት ተመሣሣይ ሁኔታዎች ለእይታ እንዲቀርብ ሊፈቀድ ይችላል።

   ቁሳቁሶች ለእይታ ከሚቀመጡባቸው አካባቢዎች በየወቅቱ ይወገዳሉ።

3. በትምህርት ዓመቱ ውስጥ በተፈቀደው ሁለት እስከ አራት ጊዜ በኤለመንተሪ ትምህርት ቤቶች ለእይታ እንዲቀመጡ ወይም እንዲሠራጩ ትርፋማ ባልሆኑ የማህበረሰብ ድርጅቶች አማካይነት የሚቀርቡ የኢንፎርሜሽን ቁሳቁሶች እና ማስታወቂያዎች ወይም በሁሉም የማህበረሰብ ድርጅቶች ወይም የቢዝነስ ድርጅቶች አማካይነት የሚሰጡ ማቴሪያሎች ቢያንስ በ10 ነጥብ ፎንት ሳይዝ/10 point font size የታተመ የሚከተለውን የስምምነት ቃል/disclaimer መስጠት-መጻፍ አለባቸው:-

   > "እነዚህ ቁሳቁሶች/ማቴሪያሎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ፣ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደት፣ ወይም በዚህ ትምህርት ቤት አማካይነት ስፖንሰር የተደረጉ ወይም የፀደቁ/የተደገፉ አይደሉም።"

4. **ለትርፍ ያልተቋቋሙ የማህበረሰብ ድርጅቶች ትርፋማ አለመሆናቸውን ማረጋገጫ ማስረጃ/ዶኩመንት ለትምህርት ቤት ማቅረብ አለባቸው። ይሄ ዶኩመንት ወይም ከ "Internal Revenue Service" ድርጅቱ በ Section 501(c)(3) መሠረት ታክስ የማይከፍል መሆኑን ማረጋገጫ ደብዳቤ ወይም የድርጅቱ አርማ ያለበት ደብዳቤ ላይ ድርጅቱ** አትራፊ ድርጅት አለመሆኑን የሚገልጽ እና የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም ያለበት/notarized ደብዳቤ መሆን አለበት።

5. **ድርጅቶች በህትመት የተዘጋጁ ቁሳቁሶችን እና ማስታወቂያዎችን እንዲሠራጩ ከታሰበበት አምስት ቀን አስቀድመው ለትምህርት ቤቱ እንዲያቀርቡ የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ሠራተኞች መጠየቅ ይኖርባቸዋል።**

6. **በህትመት የተዘጋጁ የኢንፎርሜሽን/የመረጃ ቁሳቁሶች እና ማስታወቂያዎች በጠቅላላ በ30 ቁጥር ተወስኖ**ለትምህርት ቤት ሠራተኞች አያያዝ በሚያመች ሁኔታ መከመር ያስፈልጋል።

C. **በአካባቢ ትምህርት ቤት የመተግበሪያ መስፈርቶች**

1. አትራፊ ካልሆኑ ድርጅቶች ለሚቀርቡ የመረጃ/የኢንፎርሜሽን እና የማስታወቂያ የህትመት ቁሳቁሶችን በእያንዳንዱ የኤለመንተሪ ት/ቤት ሠራተኞች እስከ 4 ቀኖች ይመድባሉ። ከእነዚያ ቀኖች አንዱ መሆን ያለበት የትምህርት ዓመት በተጀመረ 15 ቀኖች መካከል ነው። እያንዳንዳቸው ተጨማሪ ቀኖች በተለየ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ መሆን አለባቸው።

2. **የእያንዳንዱ የኤለመንተሪ ት/ቤት ሠራተኞች ለ "Office of School Support and Improvement (OSSI)" በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት ካለንደር ከጁላይ 1 በፊት የሥርጭት ቀኖችን ዝርዝር ይሰጣሉ።**

3. **የእያንዳንዱ ት/ቤት ሠራተኞች ለእይታ ወይም ለስርጭት ከተሰጡት ከእያንዳንዱ የመረጃ/የኢንፎርሜሽን ወይም የማስታወቂያ የህትመት ቁሳቁስ** አንዳንድ ቅጂ ማስቀረት አለባቸው።

4. **የትምህርት ቤት ሠራተኞች የትምህርት ቤታቸውን ወይም የበጎፈቃድ የግንኙነት መረብ እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ** ትምህርት ቤት ውስጥ ለእይታ ለማስቀመጥ ወይም ለስርጭት ሒደት።

5. **ለስርጭት ወይም ለእይታ የቀረቡት የመረጃ ወይም የማስታወቂያ ቁሳቁሶቹ ህግን ወይም የ MCPS ፖሊሲን የሚጻረር መሆኑን ሲጋት ያለበ(ባ)ት ማንኛውም ርእሰመምህር(ት) በፍጥነት ቅጂውን ለ OSSI ማቅረብ አለበ(ባ)ት። ከህግ ጋር የሚጻረሩ መረጃዊ/የኢንፎርሜሽን ቁሳቁሶች ወይም ማስታወቂያዎች** አይሠራጩም።

**ስለ ደንቡ ታሪክ፦** የቀድሞው ደንብ ቁ. 270-2፣ ሴፕቴምበር 3/1974 (የመመሪያው መረጃ ተሻሽሏል/directory information updated)፣ ጁላይ 23/1997 ተከልሷል፣ ዲሴምበር 20/2004 ተከልሷል፣ ኦክቶበር 26/2006 ከለሳ ተደርጓል፣ ሴፕቴምበር 24/2012 ተሻሽሏል።